







ከልዩ ልዩ የስዊዘርላንድ ክፍለ ሀገራት የመጡ ኢትዮጵያውያን ዛሬ በበርን ከተማ ተሰብስበው ከአምስት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ በተደረገው ምርጫ ማግሥት በወያኔ አገዛዝ የተጨፈጨፉትን ወገኖቻችን የሰማዕታት ቀን አስበው ዋሉ።

በዚሁ የመታሰቢያ ዕለት በወያኔ ለተገደሉት ፣ አሁንም በእስር ቤት ለሚንገላቱት፣ በአጠቃላይ በበሽታ፣ በርሀብና በኑሮ ችግር ለሚሰቃየው ህዝባችን የህሊና ፀሎት ተደርጎላቸዋል።

እንደሁም በቅርቡ ከእስር የተፈቱትን የሰላም አርበኛና የአንድነት ፓርቲ ሊቀ መንበር ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ተጋድሎአችውን በማድነቅና ከልጃው፣ ከእናታቸው፣ከዘመድና ከሚወዳቸውና ከሚወዱት ህዝባቸው ጋር በመቀላቀላቸው ተሰብሳቢዎች የተሰማቸውን ታላቅ ደስታ በጋለ ስሜት ገልጸዋል። ወደፊትም ለፍትህ ፣ ለዲሞክራሲና ለነፃነት በሚደረገው ትግል ወ/ሪት ብርቱካን የከፈሉት መስዋዕት በአርአያነቱ  ዘወትር በክብር ሲወሳ እንደሚኖርና ለዚህ ትውልድ ጠቃሚ ተመክሮ የሰጠ መሆኑ ተገልጿል።

ይህንኑ የሰማዕታት ቀን የሚዘክሩ ሥነ ግጥሞችና ንግግሮች የተደረጉ ሲሆን በተለይ በ 1997 ምርጫና በሰላማዊ ወገኖች ላይ ወያኔ ጅምላ ጭፍጨፋ፣ እስራትና የማቁሰል ድረጊቶችን በፈጸመበት ወቅት በቦታው የነበሩና ያዩ ግለሰብ ባቀረቡት ግጥም ላይ በወያኔ ጥይት እየተመቱ ሲወድቁ ያዩት ምንግዜም ከህሊናቸው ሊወገድ እንዳልቻለ እንባ እየተናነቃቸው ለተሰብሳቢዎች አስረድተዋል። ስለሆነም ብለዋል እኒህ ግለሰብ “ የኢትዮጵያ ስቃይ በአጭር እንዲቋጭ አገር ወዳድ ነን የምንል ኢትዮጵያዋያን በየአለንበት ቦታ በአንድነት መረባረብ ይኖርብናል ። ወገኖቻችን በወያኔ ጨካኝ ቡድን በጥይት እየተደበደቡ ፣ እየታሰሩና እየተሰደዱ የሚቀጥሉበት ሁኔታ መቆም አለበት። ወገኖቻችን በጥይት እየተደበደቡ መስዋዕት ሲሆኑ በሕይወት ያሉት ወገኖች ደግሞ የነጻነት ትግሉን መቀጠልና በአገራችን የተተከለውን ዘረኛና ገዳይ መንግሥት ለማስወገድ ሁሉም በየአካባቢው በግልና በጋራ

እንዲጥር መክረዋል። ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ቀውጢ ሁኔታ ተላቃ ነፃ እንድትወጣ እጅ ለእጅ መያያዝ አስፈላጊ ነው። የወያኔ ጥንካሬው መከፋፈላችን ስለሆነ በአዲስ መንፈስ መጠናከርና የኢትዮጵያ ድል እንዲቃረብ ማድረግ ይኖርብናል። የራሳችንን ችግር ራሳችን መወጣት አለብን ለዚህም የራሳችንን ጥንካሬ ይጠይቃል።" በማለት የሁሉንም ስሜት የሚቀሰቅስ ምክር በመስጠት በትግሉ ዙሪያ እንድንሰባሰብ አሳስበዋል።

በዚሁ ስብሰባ በወቅታዊ የአገራችን አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሀገራችን እና የወገኖቻችንን ህልውና ለአደጋ እያጋለጠ ያለውና ፍጹም ኢትዮጵያዊነት የሌለው የወያኔ መሰሪና ዘረኛ ቡድን በሚወገድበት መንገድ መሰለፍ ያስፈልጋል የሚሉ ጥሪዎች ተላልፈዋል። ወያኔ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋትና አንጡራ ሀብቷንም በመበዝበዝና ለባዕዳን አሳልፎ በመሸጥ ላይ ስለሆነ ህዝቡ በራሱ ሀገር በዘመናዊ ባርነት ውስጥ እየተዘፈቀ መሆኑን የሚያሳዩ ተጨባጭ እርምጃዎችንም ሲወስድ እያየን ነወ። በተለይ ህዝባችን በርሀብ ፣ በእርዛት ፣ በበሽታ እና በአገዛዙ ደህንነት የሚደርስበት ስቃይና መከራ ዝም ተብሎ የሚታይበት ወቅት አለመሆኑ በሁሉም ግንዛቤ ተወሳዷል።

በመጨረሻም የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ለመሳተፍ ምን መድረግ አለበት፣ ድክምቶቻችንስ ምንድን ናቸው በሚሉት ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ወይይት ተደርጓል። ወያኔ በሀገር ቤት ያለውን አፈና ወደ ውጭ ሀገርም በማስፋፋት በአሁኑ ወቅት በገሀድ የሚታዩ እንቅስቃሴዎች ማድረጉንና በተለይም የተለያዩ የኢትዮጵያውያንን ተቋማትና ድርጅቶችን ለመቆጣጠር የሚያደረገው ተንኮልና ሴራ በገሀድ እየታየ መምጣቱ ለሁሉም ግልጽ እንደሆነ ተወስቷል። ለዚህ የወያኔ እኩይ ተግባር ማስፈጸሚያነት የረዳው ደግሞ እኛው ኢትጵያውያን በድርጅት፣ በዘርና በተለያዩ ምክንያቶች መከፋፈላችን እንደሆነ ተሰምሮበታል።
እኛ በስዊዘርላንድ የምንኖር ኢትጵያውያንም በሌላው ዓለም እንዳለው ኢትዮጵያዊ የዚሁ መከፋፈል በሽታ ተጠቂዎች መሆናችንና አንድ የሀገር ማዳን አጀንዳ እያለን በአንድነት እንዳንሰለፍ ያደረጉን ምክንያቶች ስላሉ በቅድሚያ እነዚህ ችግሮች የሚወገዱበትን እርምጃ መውሰድ አለብን። ለዚህ ደግሞ እኛ ዛሬ እንጀምር ሌሎችም ከእኛው ጋር እንዲሰለፉ ልዩነቶቻችንን በውይይት እንድንፈታ ጥሪ እናስተላልፍ የሚል የመፍትሄ ሀሳብ በተሰብሳቢዎች ቀርቦ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል።

በዕለቱ የተገኙት ኢትዮጵያውያን አሁን በሀገራችን ያለው ወቅታዊ ሁኔታ ጊዜ የማይሰጠው ስለሆነ እየተካሄደ ባለው ትግል በአጋርነት ለመቆም እንዲችሉ ሁሉንም በስዊዘርላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚወክል " **በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያውያን የዲሞክራሲና የሰባዊ መብት አስተባባሪ ግብረ ኃይል** " እንዲቋቋም ስምምነት ስለተደረሰ ይኸው በዕለቱ ተግባራዊ ሆኗል። ለሀገርና ለወገን ከሚደረገው የነፃነት፣ የፍትህና የዲሞክራሲ ትግል በተጨማሪ በስዊዘርላንድ ያለውንና ጀሮ የተነፈገውን አሰቃቂ የስደት ጠያቂዎች ችግር ለመቀረፍና በጋራ ለመንቀሳቀስ ይቻል ዘንድ ከራሱ ከችግሩ ሰለባዎች የተውጣጣ ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ይኸው ኮሚቴ የሥራ ዕቅዱን በዝርዝር በቅርቡ በመግለጫ እንደሚያሳውቅ የሚጠበቅ ሲሆን በዕለቱ ተሰብሳቢዎች ስምምነት የተደረሰባቸው የኮሚቴው ዋና ዋና ተግባሮች:

1. በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረገው ፀረ ወያኔ ትግል በስዊዝ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ሆነው ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያስተባብራል። ይኸውም ሰላማዊ ሰልፎችን ያስተባብራል፣ ጥሪ ያደርጋል። የዲፕሎማሲና የሎቢ ሥራ ያካሂዳል። ስዊዝ አቀፍ የጋራ መድረኮችና ልዩ ዝግጅቶችን ያደርጋል።
2. በተለያየ ምክንያት እርስ በእርሳቸው የተጋጩ እና በተራራቁ ድርጅቶችና ግለሰቦች መካከል እርቅና ሰላም እንዲፈጠር ያደርጋል።
3. የስደተኞችን ጉዳይ ይከታተላል። በስደተኞች ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ በኩል ልዩ ልዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ የስደተኞችን ችግር ለመፍታት ጥረት ያደርጋል።

ስለዚህም በቅርቡ በአዲሱ ኮሚቴ አስተባባሪነት በስዊዘርላንድ ለሚደረገው እንቅስቃሴና የሰላም ጥረት አዎንታዊ መልስ ለመስጠትና ድጋፍና ትብብር ለማድረግ እያንዳንዱ ሰው አራሱን እንዲያዘጋጅ ተሰብሳቢዎች ጥሪአቸውን በአሁኑ ወቅት በስቃይ ላይ ባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም በማስተላለፍ የዕለቱ ዝግጅት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

## ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !

በዕለቱ የቀረቡት ሥነ ግጥሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

# የተኛው አንበሳ

ይህች የተኛው አንበሳ የምትለው ሥነ ጽሑፍ የ 5 : 45 ማስጠንቀቂያ ነች። ስዊዝ ውስጥ ሊጨልም 15 ደቂቃ ቀርቶታል ። ምዕአተኛው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ላይ ነው። ይህንን ያስተዋሉ ጠላቶቻችን ወያኔዎች በጥድፊያ ላይ ናቸው።

- ሕዝብ የሚሰባሰብበትን ቦታ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ለዘመናት የተጉበት ዘንድሮ ለጊዜውም ቢሆን በብዙ ካንቶኖች ከሞላ ጎደል የተሳካላቸው ይመስላል።
- የአንድ ለአምስት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ኃያል ከነበሩ ድርጅቶች የተቀዳ የተኮረጀ የወያኔ የጥርነፋ ሲስተም አገር አቋርጠ በስደት ቦታችንም በግልፅ እየተስተዋለ ይታያል።
- ጨለማን ተገን አድርገው የሚያከብሩት በዓላቸውን ያለፍራቻ በቀን ጀምረውታል። ስንት አንበሶች ባሉበት የጀኔቫ ከተማ ያለምንም ተቃውሞ የብኤዴን 30ኛ ዓመት በ ኖቬምበር 21 . 2010 መከበሩ አሸማቀናል።

ለዚህ ሁሉ ውርደት መነሰኤ መከፋፈላችን ነው። የሚሉ ቅን አሳቢዎች በ ኖቬምበር 28. 2010 በሚዘከረው የሰማዕታት መታሰቢያ ላይ አጀንዳ ተይዞለት ለመወያየት ባቀዱት መሰረት ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሁሉ በሚቀርቧቸው ሰዎች በግል ለማነጋገር ተጥሯል። ነገር ግን በሚያሳዝንና በሚያሳፍር መልኩ እነገሌ በጠሩት ላይ፣ እነገሌ ባሉበት ቦታ በሚል ሰንካላ ምክንያቶች ክርስትና፣ ልደት፣ ወይም ድግስ የተጠሩ ይመስል በሰማዕታት መታሰቢያ ቀን አለመገኘት ምን ማለት እንደሆነ አንባቢ ይፍረደው። ከወራት በፊት በሰዊዝ ውስጥ እንደተነገረው ፣ በዌብ ሳይቶች ማስታወቂያው እንደተለጠፈው፣ በከረንት አፌርስ ፓልቶክ ሩም ውስጥ እና በሬድዮንም በተዋወቀው፣ መሠረት በቀኑ በሚያስደስት ሁኔታ የሰዊዝ በረዶ እና ቅዝቃዜ ባልበገራቸው ኢትዮጵያውያን በተገኙበት የሰማዕታትን ቀን ለመዘከር ችለናል።

# የተኛው አንበሳ

> የተኛው አንበሳ ይነሳ ቀስቅሱት
> በንቦች ተወሮ ቀፎ ያደረጉት።
> ሉባንጃ አጭሱ ዙሪያው ይታጠን
> መድኀኒቱ ጭስ ነው ለማጥፋት ንብን ።

የካቻምና ጀግና የስዊዝ አንበሳ
እግሩን ሰባብረውት አርገውት አንካሳ
ጥርሱን አርግፈውት ሆኖ የቁም በድን
ሀኪም ባገር ጠፍቶ አክሞ የሚያድን።
ንቦች መርዝ ረጩ ሀገሩን ነደፉት
አንበሳው ተኝቶ እያለመ ቢያዩት።
በዙሪክ ማርያም በሎዛን ገብርኤል
ጀኔቫ መድኀኒዓለም ባዝል ሚካኤል
በቅዳሴም ሆነ በንግሥ በዓል ላይ
ማነው የወሰነው ባንዲራ እንዳይታይ።
በዙሪክ ማርያም የኖረ ለዓመታት
ባንዲራችን ወርዶ መጋዘን ሲከቱት
ምነው ሰው ጠፋበት በአገሩ በምድሩ
የዝምታው ብዛት ምን ይሆን ሚስጢሩ።


> የተኛው አንበሳ ይነሳ ቀስቅሱት
> በንቦች ተወሮ ቀፎ ያደረጉት።
> ሉባንጃ አጭሱ ዙሪያው ይታጠን
> መድኀኒቱ ጭስ ነው ለማጥፋት ንብን ።

ጣር ይዟት ኢትዮጵያ ስትንፈራገጥ
እኛ ተከፋፍለን በጎሳ በጎጥ
ይቅር ሳንባባል ቂም በቀል ታቅፈን
አይጡን ወያኔ አደረግነው ዝሆን።
ከአምና ካች አምና አስተውል ዘንድሮ
አይጥ ሁሉ ወጣ የኖረ ተቀብሮ።
ከጉድጓዱ ወጡ ከተወሸቁበት
እየተሳለቁ በእኛ መለያየት።
ልክ እንደ ባቢሎን እንዳንደማመጥ
ጆሮአችን ተደፍኖ ተወትፎ በጥጥ።
ተናደች ኢትዮጵያ የደም መሠረት
መሬቷም ለባዳ ህዝቡም ለባርነት።
ለማንም አልበጀ የእኛ መናከሰ
መወነጃጀሉ አንዱ አንዱን መክሰሰ።
አሉብን አደራ በታሪክ የሚወሳ
ይቅር ተባብለን አሁን እንነሳ።

**የተኛው አንበሳ ይነሳ ቀሰቅሱት**
**በንቦች ተወሮ ቀፎ ያደረጉት።**
**ሉባንጃ አጭሱ ዙሪያው ይታጠን**
**መድኀኒቱ ጭስ ነው ለማጥፋት ንብን ።**

ምን ልጠቅም እኔ ብለሽ ተሰፋ አትቁረጭ
ምን ልጠቅም እኔ ብለህ ተሰፋ አትቁረጥ
አለህ ብዙ አቅም ታሪክ ለመለወጥ።
የወያኔ ኃይሉ የጀርባ አጥንቱ
የገንዘብ ምንጭ ነው ዋና መሠረቱ።
ዶላርና ኦይሮ ነጮቹ የሚያፈሱት
ከሕዝብ ሰብሰበው መሆኑን አትርሱት።
ወደ ህዝቡ ወርደን ይህን ብናሳውቅ
ፊርማ አሰባሰበን መንግሥትን ብንጠይቅ።
ለቤተሰባችን ገንዘብ ስንልክ
ሌላ መንገድ ፈጥረን ባንጠቀም ባንክ።
እንዲሁም ሀገር ቤት ላሉን ቤተሰቦች
ዕቃ እንዳይገዙ ከወያኔ ሱቆች።
ይህንን ብንሰራ በጋራ በግልም
ያበጠው ወያኔ መተንፈሱ አይቀርም።

**የተኛው አንበሳ ይነሳ ቀሰቅሱት**
**በንቦች ተወሮ ቀፎ ያደረጉት።**
**ሉባንጃ አጭሱ ዙሪያው ይታጠን**
**መድኀኒቱ ጭስ ነው ለማጥፋት ንብን ።**

28/10/2010
ሰላምታ 5 ከከረንት አፌርስ - ስዊዘርላንድ

የ ስ ቃ ይ ጎ ዳ ና

ዛሬ በዚህ ቦታ የተገናኘነው፣
የንጹሀንን ሞት አስበን ልንውል ነው፣
ወጣት ሽማግሌ ሴት አዛውንቱ፣
በሀይል አልገዛም ብሎ በማለቱ
በወያኔ መንግስት ተመታ አናቱ
ወድቆ ተዘረጋ ተደግሞ ደረቱ።
ከታሪክ በመማር የጀግኖችን ህልፈት
ህጻናት ሳይቀሩ በተግባር አሳዩት
የወረሱትኮ ካያት ቅድማያት፣
እውነት መናገር ነው እስከለተሞት
በሀሰት ከመቆም ለራስ ወዳድ መንግስት ፣
ለመሞት መርጠዋል ከመኖር በህይወት፣
ምርጫ ተባለና በአስራዘጠኝ መቶ ሰባት፣
ወያኔ ቢያቅተው የወገን ድምጽ ማግኘት፣
አስሮ አሰቃይቶ ገደለ በጥይት ።
በፈደል ጋጋታ በቃላት እሩምታ፣
ጆሮአችን ደንቁሮ በሀሰት እንብልታ፣
እስከመቼ እንቆይ ወገን ሲንገላታ ፣
ገዳዩ ተቀምጦ ንጹህ ሰው ሲቀጣ፣
ዓለም ተለወጠ ወይስ ያምላክ ቁጣ፣

፤

ወገኑን  አሳዶ በሞት የሚቀጣ ፣

በሀገራችን ታሪክ ቀድሞ መቼ መጣ፣

ያስደሰተ መስሎ በመርዛማነቱ፣

በማጅራት ያርዳል ዘቅዝቆ  ካናቱ።

ወገን በበሽታ በረሀብ አለቀ፣

በጥይት እሩምታ ስንት ሰው ወደቀ፣

ደሙ እንደዘበት ከጎኑ ፈለቀ ፣

ባስተዳደር እጦት ስንቱ ተጨነቀ

ፍትህ ተጣሰና  ለእስራት ለግድያ ቦታውን ለቀቀ።

ወይኔ ያገሬ ሰው ምን ጉድ መጣብን

ምን አጥፍተን  ይሆን ወያኔን ጣለብን

የሰው ልጅ ሰልጥኖ በሳይንስ ሲራቀቅ ፣

የመሬቱን ትቶ የጠፈሩን ሲያደንቅ፣

በምርምር ገፍቶ ወገኑን ሳይደብቅ፣

ውጤቱም ሆነለት እጅግ የሚያስደንቅ።

አውሮፓ አሜሪካ ላንድነት ሲመከሩ፤

ላገራቸው ልማት ሲጥሩ ሲግሩ፡

በምርምር አድገው ውጤት ሲያሳምሩ ፤

ወያኔ ምን ሆነ ለጥቅም ማደሩ፤

ኸረ ምን ሆኖ ነው መግደሉ ማሰሩ፤

የወገኑን ደም በማፍሰስ መኖሩ።

እንግዲህ ወገኔ........

መሽመድመድ ሳይመጣ በጉብዝና ወራት፣
ውሸትን ከመስማት ወገንን ከማጣት፣
ፈጣሪን ሰንቀን አንድ ሆነን በመስራት፣
ባለጌውን መንግስት ከምድረገጽ ማጥፋት።
ሁላችን መልስ እንስጥ አንድላይ በሆታ
ህይወትን ተከተን በሰማእታት ቦታ።
ፈጣሪ እረድቶን ብርሃን እስኪወጣ ፣
የሞቱትን አርማ ዛሬ ተረክበን እንውጣ፣
በቃ ብለን ከልብ እንቆጣ፣
እስኪያገኘው ድረስ የፈጣሪ ቁጣ፣
ለነጻነት ትግል ብትንትኔ ይውጣ፣
የሚል ውሳኔአችን ከልባችን ይምጣ።
ፈጣሪ ብዙ ልጆች አሉህ ላንተ የተገዙ ፣
ምነው ዝም አልካቸው ተረግጠው ሲገዙ።
ሕጻን ሽማግሌ አይለይም ሴቶችን፣
አምላክ አትለየን እንደዚህ ባለው ቀን፣
ብለን እንጸልይ ውጤት እንዲኖረን፣
ማውራት ይበቃናል ከንፈር አሞጥሙጦ፣
ጊዜ ያልቃል የዛሬው በነገ ተውጦ።
ወታደር ምሁሩ ከተሜ ገጠሩ ስማኝ በጥሞና
ለነጋዴው፣ ለዘረኛው ፣ለገዳዩ መንግስት መስራት ይቁምና
በሰላማዊ ትግል መሸወድ ይብቃና

፤

ለነጻነት ፤ለፍትህ ለእኩልነት እንታገልና
ሁሉን እናድነው ከስቃይ ጎዳና ፤
ሀገራችንም ትደግ እንይ በቁመና
ብዬ ልሰናበት አምላክ ያርገን ደህና።

የኔ ኣበባ